HM Government

Grenfell community updates

Grenfell Tower community update: November 2026 - Amharic/ አማርኛ

የግሬንፌል ታወር (Grenfell Tower) ማህበረሰብ ወቅታዊ መረጃ፦ ኖቬምበር 2026

ግሬንፌል ታወር በአደጋው ከፍተኛ ጉዳት ለደረሰባቸው ወገኖች ጥልቅ የሆነ የግል ትርጉም እንዳለው እና ቦታው ለቤተሰቦች የተከበረ መሆኑን እንረዳለን።

ህንጻውን በጥንቃቄ የማፍረስ ስራ እየሰራን እያለ ወቅታዊ መረጃዎችን ልናጋራዎ እንወዳለን።
በዚህ ወቅታዊ መረጃ ውስጥ ስለሚከተሉት ጉዳዮች ዝርዝር መረጃ ማግኘት ይችላሉ፦

- **በመታሰቢያው ላይ እየተሰራ ስላለ ስራ**
- **ስለ አቧራ፣ ንዝረት እና የድምጽ ብክለት የሚደረግ ክትትል መረጃ**
- **የጤና እና ደህንነት ድጋፍ**
- **እኛን ለማነጋገር ወይም ተጨማሪ መረጃ ለማግኘት የሚረዱ መንገዶች**

ከዚህ ቀደም የተደረጉ ዝመናዎችን እዚህ መመልከት ይችላሉ፦ www.gov.uk/grenfell-community-updates

በመታሰቢያው ላይ እየተሰራ ያለ ስራ

ገለልተኛ የሆነ የዲዛይን ቡድን Freehaus፣ ከGrenfell ማህበረሰብ እና ከግሬንፌል ታወር መታሰቢያ ኮሚሽን (Grenfell Tower Memorial Commission) ጋር በመተባበር የመታሰቢያ ዲዛይኑን ሲያበለፅግ ቆይቷል። ከታቀደው ዲዛይን አካል እንደ አንዱ፣ የታወሩ 14 ዓምዶች እስከ አራተኛው ፎቅ ከፍታ ድረስ በቦታቸው እንዲቆዩ ይደረጋል፤ ይህም የመጨረሻው ዲዛይን አካል ተደርገው እንዲወሰዱ ያስችላል። ዲዛይኑ ከመጠናቀቁ በፊት ማህበረሰቡ ከFreehaus ጋር የሚነጋገርባቸው ተጨማሪ እድሎች ይኖራሉ፤ እንዲሁም በቀጥታ በሚከተሉት አድራሻዎች ልታገኟቸው ትችላላችሁ፦ hello@freehausdesign.com

የታወሩን አምዶች በቦታቸው በማስቀረት ታወሩን የማፍረስ ሥራ በጥንቃቄ ማስኬድ እንዲቻል፣ በታወሩ ዙሪያ ያለው የመወጣጫ ብረት ድጋፍ (ስካፎልዲንግ) እየተቀየረ ይገኛል። በዚህ ሥራ ወቅት፣ ታወሩ በነጭ መሸፈኛ ተሸፍኖ ይቆያል።

ስለ አቧራ፣ ንዝረት እና የድምጽ ብክለት የሚደረግ የክትትል መረጃ

መንግሥት በGrenfell Tower የሚሰራው ማንኛውም ሥራ በከፍተኛ የጥራት ደረጃ መከናወኑን ለማረጋገጥ ቁርጠኛ ነው። የማህበረሰቡ እና በቦታው ላይ የሚሰሩ ሰዎች ደህንነት እና ጤንነት ሁልጊዜም

ቅድሚያ የምንሰጠው ጉዳይ ነው። በቦታው ላይ ስለ አቧራ፣ ንዝረት እና የድምጽ ጫጫታ የቀጥታ መረጃዎችን የሚሰበስቡ የክትትል መሣሪያዎች ተተክለዋል። መረጃው በየወሩ ለሕዝብ ይፋ ይደረጋል። የቅርብ ጊዜ ሪፖርቶችን ለማየት፣ እባክዎን ከታች ያሉትን ማስፈንጠሪያዎች ይጫኑ፡-
Dust monitoring report 31 August to 27 September 2026
Vibration monitoring report 31 August to 27 September 2026
Noise monitoring report 31 August to 27 September 2026

በGrenfell Tower አካባቢ ሥራ በሚከናወንበት ወቅት፣ የUK የጤና ዋስትና ኤጀንሲ (UK Health Security Agency፣ UKHSA) የአካባቢውን የአየር ንጽሕና መገምገሙን እና መከታተሉን ይቀጥላል። ሪፖርቶቹ በየወሩ ለሕዝብ ይፋ ይደረጋሉ። የቅርብ ጊዜውን ሪፖርት እዚህ ማግኘት ይችላሉ፡-
Environmental monitoring following the Grenfell Tower fire - GOV.UK

የጤና እና ደህንነት ድጋፍ

የGrenfell የጤና እና ደህንነት አገልግሎት (Grenfell Health and Wellbeing Service) ለህጻናት እና ለአዋቂዎች የሚቀርብ፣ ከክፍያ ነጻ እና ሚስጥራዊነትን የሚጠብቅ የNHS አገልግሎት ነው። ሕንጻውን በጥንቃቄ የማፍረስ ሥራ በሚከናወንበት ጊዜ ሁሉ፣ ቤተሰባቸውን ላጡ፣ ከአደጋው በሂወት ለተረፉት እና በአቅራቢያው ለሚገኙ ነዋሪዎች የሥነ-ልቦና እና የአካል ደህንነት ድጋፍ መሰጠቱ ይቀጥላል። አንድ ሰው ማነጋገር ከፈለጉ ይህን መጠቀም ይችላሉ፡-

- በ 020 8637 6279 ለግሬንፌል ደህንነት አገልግሎት (Grenfell Wellbeing Service) ይደውሉ (ሁሌም ከ8am እስከ 8pm)።
- ድንገተኛ ሁኔታ ሲያጋጥም የማዕከላዊ እና የሰሜን ምዕራብ ለንደን የNHS ፋውንዴሽን ትረስት (Central and North West London NHS Foundation Trust’s, CNWL) የአንድ ጊዜ የምክር አገልግሎት መስመር በሚከተለው አድራሻ ይደውሉ፡- 0800 0234 650 (በቀን ለ24 ሰዓታት፣ በሳምንት ለሰባት ቀናት ክፍት ነው)።
- ኢሜይል፡- grenfell.wellbeingservice@nhs.net
- ተጨማሪ ለማወቅ ይህን ይጎብኙ፡- www.grenfellwellbeing.cnwl.nhs.uk

የሚገኙ አገልግሎቶችን በተመለከተ ወቅታዊ መረጃ ለማግኘት፣ www.grenfell.nhs.uk ን ይጎብኙ።

እንዴት ማነጋገር ወይም ተጨማሪ መረጃ ማግኘት እንደሚቻል

መረጃውን ለእርስዎ ጠቃሚ በሆነ መንገድ ማጋራት እንፈልጋለን። በየጊዜው የሚወጡ ዝማኔዎችን እና መረጃዎችን በሚከተለው አድራሻ ማጋራታችንን እንቀጥላለን፡- www.gov.uk/grenfell-community-updates

ለሚከተሉት ጉዳዮች እባክዎ በዚህ GrenfellTowerSite@communities.gov.uk ኢሜይል ያድርጉልን፡-

- እኛን ወይም የቦታው ዋና ሥራ ተቋራጭ የሆነውን DCUK ለማነጋገር ቀጠሮ ይያዙ።

- ሕንጻውን በጥንቃቄ የማፍረስ ሥራን በተመለከተ ያሉዎትን ማናቸውንም ጥያቄዎች ይጠይቁን ወይም ስጋቶችዎን ያጋሩን።
- የምናወጣቸው ወቅታዊ መረጃዎች በቀጥታ በኢሜይል እንዲላኩልዎ ይጠይቁን።
- ከእርስዎ ጋር በምናደርገው የግንኙነት እና የተሳትፎ ሂደት ላይ ያለዎትን አስተያየት፣ ፍላጎትዎ ከሆነ፣ ያጋሩን። የእርስዎን ሃሳቦች በደስታ እንቀበላለን።

ስለ ግሬንፌል ታወር (Grenfell Tower) የቅርብ ጊዜ መረጃዎችን ለማግኘት እና የኢሜይል ማሳወቂያዎች እንዲደርስዎ ለመመዝገብ፣ እባክዎን ወደ www.gov.uk/grenfell-community-updates ይሂዱ ወይም የQR ኮዱን ስካን ያድርጉ።